ጥቅምት 17 ቀን 2005 ዓ.ም

ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት
ይግባኝ ሰሚ ችሎት
አዲስ አበባ

ይግባኝ ባዮች ---------- 1ኛ/ አውላቸው ደቻሳ አባተ

2ኛ/ ወ/ሮ ስንታየሁ ደመቀ ወርቁ

መልስ ሰጭ ---------- ወ/ሮ አመለወርክ ተስፋዬ በርሄ

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ **3** ኛ የፍትሐብሔር ችሎት በመዝገብ ቁጥር **36745** ጥቅምት **9** ቀን **2005** ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት በፍ/ብ/ሥ/ህግ ቁጥር **327** መሰረት የቀረበ የይግባኝ አቤቱታ

ሀ. የጉዳዩ መነሻ ፍሬነገርና ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በአጭሩ

1. ይግባኝ ባዮች ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የመኪና ሽያጭ ውል የሰሌዳ ቁጥሩ 01-16971 አ.አ ፣የሻንሲ ቁጥሩ JTIWYH61V00072386፣የሞተር ቁጥሩ 3Y-0707474 የሆነ አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ መኪና (ታክሲ) 200000.00 ብር በመክፈል ከመልስ ሰጭ ላይ ገዝተው ነበር። ሆኖም ግን የመኪናውን ስመ-ንብረት ወደ 2ኛዋ ይግባኝ ባይ ስም ለማዞርና የመኪናውን ኮድ ከኮድ 01 ወደ ኮድ 03 ለመቀየር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የትራንስፖርት ባለስልጣን ለአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ጥያቄው በይግባኝ ባዮች ሲቀርብ የጽ/ቤቱ ባለሞያዎች መኪናውን ሲመረምሩ የመኪናው ሻንሲ ተቆርጦ የገባ (የተቀጠለ) መሆኑንን አረጋግጠው እንዲህ ያለው መኪና ወደ ኮድ 03 ተለውጦ መደበኛ ታርጋ የሚሰጠው ሳይሆን ቀይ ሰሌዳ ብቻ ሊያወጣ እንደሚችል ጽ/ቤቱ ለይግባኝ ባዮች ገልጾላቸዋል።
2. ይግባኝ ባዮችም ግዢውን ሲፈጽሙና ገንዘቡን ለመልስ ሰጭ ሲከፍሉ መኪናው እንዲህ ያለ መሰረታዊ ችግር ያለበት መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ ግዢውን እንደማይፈጽሙ በመግለፅ መልስ ሰጭ ከይግባኝ ባዮች ላይ የወሰደችውን 200000.00 ብር በመመለስ መኪናዋን መውሰድ እንደሚገባት ገለጹላት። ይሁን እንጂ መልስ ሰጭ መኪናዋን በመውሰድና ከይግባኝ ባዮች ላይ የወሰደችውን ገንዘብ ለመመለስ ፈቃደኛ ልትሆን ባለመቻሏ ይግባኝ ባዮች ውሉ ይፈርስ ዘንድ /Invalidation/ በሥር ፍ/ቤት ክስ መሰረቱባት። ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሲያዳምጥ ቆይቶ ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል። ፍ/ቤቱም ይግባኝ ባዮች ውል ይፍረስልን በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ከዋቢነተ ጽንሰሃሳብ ጋር /Warranty/ ጋር በማደባለቅና በማምታታት ይግባኝ ባዮች ያቀረቡት ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ሲል ወስኗል። ሆኖም ግን የፍ/ቤቱ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ በመሆኑ በጥብቅ እንቃወመዋለን። የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ ስህተት ያለበት ውሳኔ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ውድቅ መደረግ አለበት የምንልበትን ምክንያት ከዚህ በታች እንደሚከተለው በዝርዝር እናቀርባለን።

ለ. ይግባኝ ባዮች የሥር ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ያሏቸው የቅሬታ ነጥቦች

1. የአሁን ይግባኝ ባዮች /የሥር ከሳሾች/ በሥር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት የመኪና ሻንሲ ተቆርጦ መግባቱን ሳያውቁ ውል በመግባታቸው ይህ ደግሞ መሰረታዊ የሆነ ስህተት በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በሚል ነው። የሥር ፍ/ቤት ግን ውሉ ሲደረግ መሰረታዊ ስህተት ነበር ወይስ አልነበረም የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ይግባኝ ባዮች ያቀረቧቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ትክክለኛውን ጭብጥ በመተው ወደ ዋቢነት ጥያቄ መሄዱ አግባብ አይደለም። ምክንያቱም የተከበረው ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንደሚገነዘበው ማንም ሰው መኪና የሚገዛው ተሽከርካሪው አንድ ተሽከርካሪ ሊያሟላቸው የሚገባውን ነገሮች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነው። አንድ ተሽከርካሪ ተሽከርካሪ ሊባል የሚችለው ደግሞ ሻንሲው ጤናማ ሲሆን ነው። ለምን ቢባል የመኪናው ሻንሲ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነ ነገር ስለሆነ ነው። የአንድ መኪና ሻንሲው ተቆርጦ ገባ ማለት አንድም መኪናው ወንጀል ተፈፅሞበታል፣ ወይም የተሰረቀ መኪና ነው ፣ ወይም ደግሞ ተገቢውን የመንግስት ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ገባ ነው ማለት ነው። በመሆኑም ይግባኝ ባዮች የመኪናውን ግዢ ሲፈፅሙ የመኪናው ሻንሲ ተቆርጦ የገባ መሆኑን ቢገነዘቡ ኖሮ መኪናው ከላይ የተመለከቱት ችግሮች ያሉበት መሆኑን ለመረዳት ስለማያዳግታቸው ግዢውን አይፈፅሙም ነበር።
2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 በተጠቀሰው ምክንያት ይግባኝ ባዮች ሻንሲው የተቆረጠ መኪና በመግዛታቸው መሰረታዊ ስህተት ተፈጽሟል ማለት ነው። ስለዚህ በእንዲህ ዓይነት ሁኔት የተፈፀመ ውል ደግሞ የይግባኝ ባዮችን ውል የመዋዋል ነፃ ፈቃድ የጣሰ ነው። በፍትሐብሔር ህጋችን በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ሰው በህግ ፊት የሚፀና ውል ተዋዋለ የሚባለው ውሉን ያደረገው በነፃ ፍቃዱ

የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው። አለበለዚያ አንድ ሰው ውል የተዋዋለው የፍቃድ መጓደል /Vice of consent/ በኖረበት ሁኔታ የሆነ እንደሆነ ውሉ ሊፈርስ እንደሚገባው በፍ/ብ/ህጋችን በግልፅ ተደንግጓል። በመኪና ግዥ ውል ደግሞ የሻንሲው ደህንነት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ማንኛውም ሰው ሻንሲው የተቆረጠ መኪና ሻንሲው መቆረጡን ሳያውቅ ከከዛ መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሟል ማለት ነው። ስለዚህ እንዲህ ለው ውል ደግሞ ገና ከአመሰራረቱ መሰረታዊ እንከን ስለገጠመው የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ተሳስቻለሁ በሚለው ወገን ከቀረበ ውሉ መፍረስ ነው የሚኖርበት።

3. አሁን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ የተከበረው ግባኝ ሰሚ ችሎት እንደሚረዳው ማንም ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው ቢሆን የሚገዛው መኪና ሻንሲው ተቆርጦ ገባ መሆኑን እያወቀ የመኪና ግዥ ውል ሊፈፅም አይችልም። ምክንያቱም እንድህ ያለው መኪና (ሻንሲው የተቆረጠ መኪና) ሊሸጥና ሊለዋወጥ የማይችል ስለሆነ ስለሚሸከረከር ብቻ መኪና ተብሎ ሊጠራ አይችልምና ነው። እንደሚታወቀው ማንም ሰው አንድ ንብረት የሚገዛው ሲያሻው ታርጋውን ለውጦ ሊጠቀምበት፣ሊሸጠው ወይም ሊለውጠው አልም ደግሞ በስጦታ ሊያስያስተላልፈው፣ በመያዣ ሊሰጠው ወይም ደግሞ በሌላ በማናቸውም ህጋዊ ህጋዊ መንገድ ሁሉ በመብቱ ሊሰራበት ነው። በዚህ ይግባኝ የተመለከተው መኪና ግን ሻንሲው የተቆረጠ በመሆኑ ይግባኝ ባዮች በእነዚህ መብቶች ሊሰሩባቸው አይችሉም። ስለዚህም ይግባኝ ባዮች የመኪናው ሻንሲ ተቆርጦ የገባ መሆኑን ግዥቸውን ሲፈፅሙ አውቀው ቢሆን ኖሮ እንዲህ ያለ የግዥ ውል ሊፈጽሙ አይችሉም ነበር። ለምን ቢባል ይህንን ያክል ገንዘብ አውጥተው ሻንሲው የተቆረጠ፣ ሊሸጥና ሊለወጥ ማይችል፣ መደበኛ ታርጋ ሊሰጠው የማይችል መኪና ይገዛሉ ተብሎ በፍፁም ሊታሰብ ስለማይቻል ነው።

4. መልስ ሰጭ በሥር ፍ/ቤት አጥብቃ የተከራከረችው ይግባኝ ባዮች የመኪናውን ግዥ ሲፈፅሙ መኪናውን በመረጡት ጋራዥ ያስመረመሩት በመሆኑ ውሉ ይፍረስልኝ የማለት ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም የሚል ነው። የሥር ፍ/ቤቱም ይህንን ክርክር በመቀበል ይግባኝ ባዮች ተሸከርካሪውን ከተከሳሽ /ከአሁን መልስ ሰጭ/ በሚገዙበት ጊዜ ሻንሲው የተቆረጠ ስለመሆን አለመሆኑ ሳያረጋግጡ ግዥ ከፈፀሙ በኋላ ጉድለት አለበት ማለታቸው አግባብነት የለውም በማለት ወስኗል። ነገር ግን የመልስ ሰጭ ክርክርም ሆነ የፍ/ቤቱ ውሳኔ ፍፁም የህግ መሰረት የሌለው ነው።ምክንያቱም ይግባኝ ባዮች መኪናውን ሲገዙ መኪናው በጋራዥ የተመረመረ መሆኑ ባይካድም መኪናውን የመረመረው ባለሞያ የመኪናው ሻንሲ ተቆርጦ የገባ መሆኑን አላመለከታቸውም። ይህም ሊሆን የቻለው መኪናውን የመረመረው ባለሙያ የመኪናውን ሻንሲ መቆረጥና አለመቆረጥ ያላረጋገጠ በመሆኑ ነው። ሻንሲው የተቆረጠ መሆንና አለመሆኑን ጥረት ቢያደርግ ኖሮ እንኳ ሻንሲው የተቆረጠ መሆኑን ላይገነዘበው ይችላል። ይህንንም የምንልበት ምክንያት ማንኛውም መካኒክ /ጋራዥ/ የአንድ መኪና ሻንሲ ተቆርጦ የገባ መሆን አለመሆኑን ለመኪና ምርመራ ሲያደርግ መገንዘብ የሚችልና የማይችል መሆኑን ለፍ/ቤቱ እንዲፅፍ በፍ/ቤቱ የታዘዘው ሐኒቤስ ኃላፊነቱ የተወሰነ ግል ኩባንያ ሐምሌ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ መኪና ምርመራ የሚያደርጉ መካኒኮች ሽያጭ በሚከናውንበት ወቅት የሞተር ቁጥሩና የሻንሲው ቁጥር ከሊብሬው ጋር መገናዘቡን ፣ በይበልጥ ደግሞ የሞተሩን ቴክኒካዊ ይዘትና ውጫዊ አካል ላይ ትኩረት ሰጥተው ምርመራ እንደሚያካሂዱ ፣ ሆኖም ግን በሜካኒክ ሞያ አሰራር የሻንሲ ምርመራው መጣመም አለመጣመሙ ላይ እንጂ ቁጥሩ ተቆርጦ የገባ መሆን አለመሆኑ ላይ ምርመራ በማድረግ ችግሩን መለየት የሚችሉት ልምድ ያላቸው ባለሞያዎች ብቻ ሲሆኑ ወይም ደግሞ እንዲመረምሩ ሲጠየቁ ነው በማለት የማያሻማ መልስ ሰጥቷል።

5. የሥር ፍ/ቤር ግን ሐኒቤስ ኃ/የተ/የግ ማህበር የሰጠውን ቀጥተኛና ግልፅ መልስ በውሳኔው አዛብቶ ነው ያተተው። ምክንያቱም ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሳኔ ከገፅ 2-3 ያለውን በማንበብ እንደምንረዳው ፍ/ቤቱ <u>ሐኒቤስ ኃ/የተ/የግል ማህበር በፃፈው ምላሽ አንድ መኪና በሽያጭ ወቅት በመካኒክ ፍተሻ ሲደረግለት መካኒኩ ሻንሲው ተቆርጦ የገባ መሆኑን ለማወቅ የሚቻል ሲሆን</u> ---በማለት አትቷል። ሆኖም ግን የተከበረው ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሐኒቤስ ኃ/የተ/የግ ማህበር በ 22/11/2003 ዓ.ም ለሥር ፍ/ቤት የፃፈውን ደብዳቤ ሲመለከት እንደሚገነዘበው ሐኒቤስ ኃ/የተ/የግ ማህበር የሰጠው ምላሽ የሥር ፍ/ቤት በውሳኔው ካሰፈረው በተቃራኒው ነው። ከምንም በላይ ደግሞ የመኪናው ሽያጭ ውሉ ሲደረግ መኪናውን የመረመረው ባለሙያ(አቶ አስራት አብርሃም የተባለው የይግባኝ ባዮች 1 ኛ ምስክር) ለሥር ፍ/ቤት በሰጠው ምስክርነት ቃል በወቅቱ መኪናውን ሲመረምር የሻንሲ ምርመራ እንዳላደረገና ሻንሲው ተቆርጦ የገባ መሆኑን እንዳላረጋገጠ ለፍ/ቤቱ አስረድቷል። ሆኖም ግን የሥር ፍ/ቤት የዚህን ግለሰብ የምስክርነት ቃል በውሳኔው ውስጥ አልጠቀሰውም። በመሆኑም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በማስረጃ ያልተደገፈና መሠረታዊ ግድፈት ያለበት በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ሊሻር የሚገባው ውሳኔ ነው።

6. የሥር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ተሸከርካሪው ታህሳስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም ፖልሪየስ በሚባለው ድርጅት ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲደረግለት ጉድለት እንዳለበት አልተመለከተም በማለት ወስኗል። ይሁን እንጂ ይህ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ይግባኝ ባዮች ያቀረቡትን ማስረጃ ፈፅሞ የተወና ያለማስረጃ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ውድቅ መደረግ አለበት። ምክንያቱም በ 2 ኛዋ ይግባኝ ባይና በመልስ ሰጭ መካከል ታህሳስ 1 ቀን 2003 ዓ.ም የመኪናው ሽያጭ ውል ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ መኪናው ይቀመጥ ነበረው አፍንጮ በር በሚገኘው "<u>አስራት ጋራዥ</u>" ውስጥ ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ታህሳስ 2003 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ መኪናው ከዚህ ጋራዥ እንዳልወጣና የትም እንዳልተንቀሳቀሰ ይግባኝ ባዮች ምስክር አስቀርበው አስረድተዋል። በመሆኑም ፖልሪየስ የተባለው ድርጅት መኪናው የቴክኒክ ችግር የለበትም ሲል ታህሳስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም ለአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅ/ፅ/ቤት የፃፈው መኪናውን በአካል ሳይመረምር ነው። መኪናው ታህሳስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም በአካል ወደ ፖልሪየስ እንዳልተወሰደ ደግሞ መኪናው ይቆምበት የነበረው የጋራዥ ባለቤት (አቶ አስራት አብርሃም) በይግባኝ ባዮች በኩል ፍ/ቤት በመቅረብ በመሃላ ሥር ሆኖ በሰጠው የምስክርነት ቃል ያረጋገጠው ህቅ ነው።የሥር ፍ/ቤት ግን ራሱ የተቀበለውንና በመዝገቡ ያሰፈረውን የምስክርነት ቃል ወደ ጎን በመተው መኪናው በታህሳስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም ወደ ፖልሪየስ ድርጅት በአካል ሄዶ እንደተመረመረና ምንም ጉድለት የለበትም እንደተባለ አድርጎ

በውሳኔው አስፍሯል። ይህም የሚያመለክተው የሥር ፍ/ቤት ይግባኝ ባዮች ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በዘፈቀደ በመተው ምንም የሕግና የማስረጃ መሰረት የሌለው ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ነው። በመሆኑም እንዲህ ያለ ከፍተኛ ግድፈት ያለበት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ሊታረም የሚገባው ውሳኔ ነው።

7. በሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ገጽ 6 ላይ በግልፅ እንደተመለከተው ይግባኝ ባዮች ውሉ ሊፈርስልን ይገባል በማለት የጠየቁት የተሸከርካሪውን ታርጋ ከኮድ 01 ወደ ኮድ 03 ለመቀየር የማይቻል በመሆኑ ነው ብለዋል በማለት አትቷል።ሆኖም ግን ይህ የፍ/ቤቱ ድምዳሜ የይግባኝ ባዮችን አጠቃላይ የክስ መንፈስና የተጠየቀውንም ዳኝነት ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም ይግባኝ ባዮች ውሉ እንዲፈርስላቸው የጠየቁት የመኪናው ሻንሲ የተቀረጠ መሆኑን የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅ/ፅ/ቤት ጥር 17 ቀን 2003 ዓ.ም ምርመራውን አድርጎ ስላረጋገጠላቸው ነው።በመሠረቱ ይግባኝ ባዮች መኪናውን ሲገዙ የመኪናውን ሰሌዳ 01 (ለታክሲ የሚያገለግል) ነበር። ሆኖም ግን ገዥዎች (ይግባኝ ባዮች) ኮዱን ወደ 03 ቀይረው ለመጠቀም ስለፈለጉና ይህም ፍፁም የሆነና በህግ የተረጋገጠ መብታቸው በመሆኑ የመኪናው ኮድ ወደ 03 እንዲለወጥላቸው ለትራንስፖርት ቅ/ፅ/ቤቱ ሲያመለክቱ የመኪናው ኮድ ከመቀየሩ በፊት በመኪናው ላይ ሙሉ ምርመራ ማድረግ ስለሚስፈልግ የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ምርመራውን በማድረግ የመኪናው ሻንሲ ተቀርጦ እንደገባ አረጋግጠውላቸዋል።ከዚህ በመነሳት ይግባኝ ባዮች በበኩላቸው መኪናውን የገዙት በስህተት መሆኑን ተገንዝበዋል። በመሆኑም ይግባኝ ባዮች የመኪናው ሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው የሚጠይቁት የመኪናው ሻንሲ መቀረጡን ሳያውቁ መኪናውን መግዛታቸው <u>በራሱ ውሉ እንዲፈርስላቸው ለመጠየቅ የሚያስችላቸው በቂና ብቸኛ ምክንያት በመሆኑ ነው</u>። ይግባኝ ባዮች መኪናውን ለታክሲ አገልግሎት ሊጠቀሙበት ይችላሉ ቢባል እንኳ ማንም ሰው ቢሆን ሻንሲው የተቀረጠ መኪና ይገዛል ተብሎ ስለማይጠበቅ ይግባኝ ባዮች በማናቸውም መልኩ የመኪናው ሽጭ ውል እንድፈርስ ተብሎ እንዲወሰንላቸው መጠቃቸው በህግም ሆነ በአመክንዮ የሚደገፍ ነው። ስለዚህ የሥር ፍ//ቤት የተሳሳተ ግንዛቤ በመያዝ የሰጠው ውሳኔ ሊሻር የሚገባው ነው።

8. የሥር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2289(ሀ) መሠረት ሽያጩ ጉድለት የሌለበት በመሆኑ ሊፈርስ አገባውም ሲል የሰጠው ውሳኔ በእጅጉ የሚነቀፍ ነው። ምክንያቱም የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 2289(ሀ) ተጠቅሶ የዋቢነት ጉዳይ የሚነሳው አሁን በተያዘው ጉዳይ አይደለም። የዋቢነት ጉዳይ /Warranty against defect/ የሚነሳው ውሉ የውል መለኪያዎችን አሟልቶ የተቋቋመ ውል ቢሆን ኖሮ ነው። ይግባኝ ባዮች ክስ የመሰረቱት ጉድለት ያለበት መኪና ይስተካከልልን በሚል ሳይሆን በስህተት የተደረገ ውል ይፍረስልን በማለት ነው። በመሆኑም የይግባኝ ባዮች ጥያቄ መኪናውን የገዛነው በነፃ ፈቃዳችን ሳይሆን እጅግ መሰረታዊና ወሳኝ በሆነ ስህተት ላይ ወድቀን በመሆኑ ውሉ ሊፈርስልን ይገባል የሚል ነው። በማናቸውም መልኩ ቢሆንም ግን የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት አይኖረውም። ምክንያቱም ማንኛውም ሻንሲው የተቀረጠ መኪና የገዛ ሰው ይህንን መኪና እንደያዘ ይቀራል ተብሎ ሊፈረድበት የሚያስችል ምንም ዓይነት የህግም ሆነ የሞራል መነሻ ሊኖር አይችልምና ነው። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በየትኛውም መለኪያ ቢታይ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።

ሐ. <u>ይግባኝ ባዮች ከተከበረው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚጠይቁት ዳኝነት</u>

1. ይግባኝ ባዮች የመኪናውን ግዢ የፈፀሙት በስህተት በመሆኑ ፣ በስህተት የተፈረመ ውል ደግሞ በህግ ፊት እንደማይፀና በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1996 እና 1808 የተመለከተ በመሆኑ ፣ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ የመኪና ሽያጭ ውል ፈርሶ መልስ ሰጭ ከይግባኝ ባዮች ላይ የወሰደችውን 200,000.00 ከህጋዊ ወለድ ጋር በመመለስ መኪናውን እንድትረከብ ተብሎ እንዲወሰንልን በአክብሮት እናመለክታለን።
2. ይግባኝ ባዮች መኪናውን ከመልስ ሰጭ ከተረከቡ ጀምሮ ሻንሲው የተቀረጠ መሆኑን እስካወቁበት ጊዜ ከመኪናው ጋር በተያያዙ ያወጡትን 9,913.00 /ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሶስት ብር/ መልስ ሰጭ እንዲትተካ ተብሎ እንዲወሰንልን በማክበር እናመለክታለን።
3. ይግባኝ ባዮች በዚህ ክርክር ሳቢያ በሥር ፍ/ቤትና በዚህ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያወጧቸውን ማናቸውም ወጪዎች መልስ ሰጭ እንዲትተካ ተብሎ እንዲወሰንልን በማክበር እናመለክታለን።

ይህ የይግባኝ አቤቱታ በእውነት የቀረበ መሆኑን ብፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 92(1) መሰረት አረጋግጣለሁ።